ቁጥር OFAG.P 02.13/3/27
ቀን 19/08/2015

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለክብርት ዶ/ር ሊያ ታደሰ
የጤና ሚኒስትር
<u>አዲስ አበባ፣</u>

መ/ቤታችን በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት የፋይናንሻልና ህጋዊነት እንዲሁም የክዋኔ ኦዲት የሚያከናውን መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሠረት መ/ቤታችን የፌዴራል ሆስፒታሎች የሕክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሠጣጥ አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የአሠራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን ለይቶ በማውጣት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለመስጠት የክዋኔ ኦዲት ማካሄዱ ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሠረት ለክዋኔ ኦዲቱ የሚጠቅሙ ማስረጃዎች በዋናው መ/ቤት ተሰብስበው ከተገመገሙ በኋላ ኦዲቱ ተጠናቆ የተገኘውን ውጤትና የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ የያዘ ረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት በደብዳቤ ቁጥር OFAG.P-02.13/3/26 በቀን 06/06/2015 ዓ.ም መላካችን ይታወሳል፡፡

በመሆኑም በተላከው የረቂቅ ሪፖርት ደብዳቤ ላይ እና በተደጋጋሚ በቃል የመውጫ ስብሰባ እንዲዘጋጅልን የጠየቅን ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመውጫ ስብሰባ እንዲደረግ ሁኔታውን ባለማመቻቸቱ ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ የሰጣችሁትን ምላሽ ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ <u>35</u> ገጽ ሪፖርት እና <u>5</u> ገጽ አባሪ በድምሩ <u>40</u> ገጽ የመጨረሻ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን ሲሆን በመ/ቤታችን የማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም መሰረት ሪፖርቱን በዓመታዊ ሪፖርታችን ውስጥ በማካተት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምናቀርብ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

መሠረት ዘሪሁን

በተጨማሪም በተላከላችሁ የኦዲት ሪፖርት ውስጥ በኦዲት ወቅት የተገኙ ዋና ዋና የአሰራር ክፍተቶችንና ድክመቶችን አስመልክቶ የማስተካከያ እርምጃዎችን በመውሰድ አሰራሩ ሕግን የተከተለ ግልጽ እና ውጤታማ ማድረግ ይጠበቅባችኋል፡፡

ስለዚህ ለክትትል ያመቸን ዘንድ መ/ቤታችሁን በተመለከተ በተደረገው የክዋኔ ኦዲት ወቅት የተሰጣችሁን የማሻሻያ ሃሳቦች ተግባራዊ የምታደርጉበትን መርሀ ግብር ከዚህ ደብዳቤ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ መሠረት ነድፋችሁ በአስራ አምስት የስራ ቀናት እንድታሳውቁን እናሳስባለን፡፡

ከማክበር ሰላምታ ጋር

**ጳውሎስ ዘሪሁን አታለል**
**የልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች**
**ክዋኔ ኦዲት ዳይሬክቶሬት**
**ዳይሬክተር**

## በክዋኔ ኦዲት ሪፖርት የተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሣቦች አተገባበር መርሐ-ግብር

የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ስም ______________________

የክዋኔ ኦዲቱ አርዕስት ______________________

መርሃ-ግብሩ የተዘጋጀበት ቀን ______________________

| ተ.ቁ. | የኦዲትግኝቶች | የተሰጡ ማሻሻያ ሃሣቦች | እስከ አሁን የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች | ቀሪ ማሻሻያ ሃሣቦች ተግባራዊ ሚደረጉበት ጊዜ | ኃላፊነት የተሰጠው የሥራ ክፍል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ይህን መርሃ-ግብር እና የተወሰዱ እርምጃዎች የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤትዎ እንደደረሰ በ15 ቀናት ውስጥ ተሞልቶ ለመ/ቤታችን ካልተመለሰ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በምናቀርበው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ "ለኦዲት ሪፖርት ማሻሻያ ሀሣቦች አተገባበር መርሃ -ግብር መልስ ያልላኩ መ/ቤቶች" ዝርዝር ውስጥ እና በማሻሻያ ሀሳቡ መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ ተጠቅሶ ለም/ቤቱ ሪፖርት የሚቀርብ መሆኑን እንገልፃለን፡፡


# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

**በጤና ሚኒስቴር**

**የፌዴራል ሆስፒታሎች የሕክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሠጣጥ አፈፃፀምን**

**በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት**




ሚያዚያ 2015 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>


# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

**በጤና ሚኒስቴር**

**የፌዴራል ሆስፒታሎች የሕክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሠጣጥ አፈፃፀምን**

**በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት**



ሚያዚያ 2015 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

# ማውጫ


**ማውጫ** ........ I

**የክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ (EXECUTIVE SUMMERY)** ........ 1

**ክፍል አንድ** ........ 5

መግቢያ ........ 5

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ ........ 5

*ራዕይ* ........ 5

*ተልዕኮ* ........ 6

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር ........ 6

ለጤና ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት ........ 7

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል ........ 8

ድርጅታዊ መዋቅር ........ 8

የሰው ኃይል ........ 8

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 9

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ........ 10

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (POTENTIAL AUDIT AREA) ........ 10

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (AUDIT ISSUES) ........ 10

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ........ 11

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 11

**ክፍል ሁለት** ........ 12

**የኦዲት ግኝቶች** ........ 12

*የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ፖሊሲ፣ መመሪያ እና ስትራቴጂ ማዘጋጀትን በተመለከተ፣* ........ 12

*የሕክምና መሳሪያዎች ግዥን በተመለከተ፤* ........ 13

*የህክምና መሳሪያዎች ስፔስፊኬሽን ዝግጅት በተመለከተ፤* ........ 14

*የህክምና መሳሪያዎች ግዥ ለጠየቁት አካላት የደረሱ ስለመሆኑ፣* ........ 14

*የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን በቅንጅት መገልገልን በተመለከተ፤* ........ 15

*የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ማድረግን በተመለከተ፤* ........ 16

*በየሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎችን ሁኔታ የሚከታተል የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ መኖሩን በተመለከተ፤* ........ 17

*በእርዳታ የሚገቡ የህክምና መሳሪያዎች ርክክብ ከመደረጉ በፊት በህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ መረጋገጡን በተመለከተ፤* ........ 18

*በየሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሳሪያዎች በመደበኛነት የደህንነት ፍተሻ እየተደረገላቸው መሆኑ በተመለከተ፤* ........ 20

*የሕክምና መሳሪያዎች የሚጠገኑበት ማዕከልን በተመለከተ፤* ........ 21

*የሕክምና መሳሪያዎች አወጋገድ መመሪያን በተመለከተ፣* ........ 22

*የሚወገዱ የህክምና መሳሪያዎች ተለይተው የሚቀመጡበት ቦታን በተመለከተ፤* ........ 24

*በየሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሳሪያዎች ያሉበት ወቅታዊ ሁኔታ መረጃ መያዝን በተመለከተ፤* ........ 26

*የህክምና መሳሪያዎችን በተመለከተ ከሆስፒታሎች እና ሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ማቀዱን በተመለከተ፤* ........ 28

*ለባለሙያዎች የሚሰጥ የክህሎት ስልጠናን በተመለከተ፤* ........ 29

**ክፍል ሶስት** ........ 30

**መደምደሚያ** ........ 30

**ክፍል አራት** ........ 33

**የማሻሻያ ሃሳቦች** ........ 33

አባሪ 1፡ የጤና ሚኒስቴር መዋቅር ........ 36
አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (EVALUATIVE CRITERIA) ........ I
አባሪ 3፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ ሆስፒታሎች ዝርዝር ........ IV

# የክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ (Executive Summery)

የዜጎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እንዲሁም የሀገሪቱን የወደፊት የልማት አቅጣጫ ግምት ውስጥ ያስገባ መከላከልን መሰረት ያደረገ የጤና ፖሊሲ አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ በዚህም መሰረት መንግስት ለጤና አገልግሎት መስፋፋት ልዩ ትኩረት በመስጠትና ህዝቡን በተደራጀ መልኩ ለማሳተፍ የዘርፉን ስራ ማሳድግ ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ ሥራ ውስጥ የጤና ተቋማትን በተገቢው የህክምና መሣሪዎች እንዲደራጁ በማድረግ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ነው፡፡

በዚህ መሰረት የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በጤና ሚኒስቴር የፌዴራል ሆስፒታሎች የሕክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ክፍተቶችን እና የችግሮቹን መንስኤ ለመለየት የክዋኔ ኦዲት አካሂዷል፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በፌዴራል ሆስፒታሎች (ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆኑትና ያልሆኑትን ጭምር) የህክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ያሉ ችግሮች እንዲለዩ እና የተለዩት ችግሮች የሚፈቱበት ስልት እንዲነደፍ የማድረግ ሥራዎች ቀልጣፋ መሆናቸውን፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ስለ ህክምና መሳሪያዎች ያወጣቸው ደረጃዎች (ስታንዳርዶች) በትክክል ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ክትትል እና ድጋፍ ማድረጉን እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን ሲሆን፣ ይህን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦች ማቅረብ ነው፡፡

ከላይ ለተጠቀሰው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሶስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም፡-

1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽ፣ ጥራቱን የጠበቀና ቀልጣፋ እንዲሆን የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፣

2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሣሪያዎች በአግባቡ እየሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣

3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በህክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ከሆስፒታሎች እና ሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ያለው የመረጃ ልውውጥ እና ቅንጅታዊ አሰራር ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣

የሚሉ ናቸው፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፉ የዋና ኦዲተሮች መ/ቤት ማህበር (INTOSAI) የተዘጋጀውን አለም-አቀፍ የክዋኔ ኦዲት ስታንዳርድ (ISSAI) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ሲሆን በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገር አቀፍ የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ፖሊሲ፣ መመሪያ እና ስትራቴጂ አዘጋጅቶ በማፀደቅ ለሚመለከታቸው አካላት ያላሰራጨ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሆስፒታሎችን የህክምና መሳሪያ ፍላጎት በመጠየቅ እና በቅድሚያ በአመታዊ የግዢ እቅድ ውስጥ በማካተት ግዥ የማያከናውን መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለጤና ተቋማት (ለሆስፒታሎች) የተላከላቸው የህክምና መሳሪያዎች በትክክል ስለመድረሳቸው ክትትል የሚያደርግበት ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ለማድረግ የሚረዳ የረጅም ጊዜ ዕቅድ ቢያዘጋጅም የሚደረስበት ኢላማና የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ሆስፒታሎች በእርዳታ የሚገቡ የህክምና መሳሪያዎች ርክክብ ከመደረጉ በፊት በህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ ወይም በሆስፒታሎች ማኔጅመንት እየተረጋገጠ ርክክብ የሚደረግ ስለመሆኑ የሚከታተልበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች በስራ ላይ ያሉ ህክምና መሳሪያዎች መደበኛ የፍተሻ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ባለሙያ የደህንነት ፍተሻ (inspection and testing) እያስደረጉ ስለመሆኑ ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሳሪያዎች ለመሣሪያዎቹ በተቀመጠው የጊዜ መሰረት ትክክለኛነታቸውን በየጊዜው ለማረጋገጥ

የመለካት (Calibration) ስራ ስለመስራት አለመስራታቸው ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

- ከአንድ የህክምና መሳሪያ ወደ ሌላ የህክምና መሳሪያ በመውሰድ እንደመለዋወጫ መጠቀም የሚያስችል መመሪያ በቅድሚያ ሳይዘጋጅ ሆስፒታሎች ከአንድ መሳሪያ እቃ ወስደው ወደ ሌላ መሳሪያ የሚገጠሙ መሆኑ፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከላይ የተጠቀሱትን የኦዲት ግኝቶች ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገር አቀፍ የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ፖሊሲ፣ መመሪያ እና ስትራቴጂ አዘጋጅቶ በማጽደቅ፣ ለሚመለከታቸው አካላት በማሰራጨት ተግባራዊ ማድረጋቸውን በየጊዜው በእቅድ በመያዝ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሆስፒታሎችን የህክምና መሳሪያ ፍላጎት በመጠየቅ እና በመሰብሰብ በዓመታዊ የግዥ እቅድ ውስጥ በቅድሚያ በማካተት ለመሣሪያዎቹ ተገቢውን ስፔሲፊኬሽን በማዘጋጀትና ግዥውን በተፈቀደው የግዥ ሥርዓትን በመጠቀም ግዥው መከናወኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ የተገዙትንም የህክምና መሣሪያዎች በተጠየቀው ስፔሲፊኬሽን መሠረት መሆኑን የሚረጋግጥበት ሥርዓት ሊዘረጋ፣ መሣሪያዎቹ ለጠየቁት አካል መድረሱን እና ርክክብ ተፈጽሞ በተቋማቱ ንብረትነት መመዝገቡን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ10 ዓመት የጤና ዘርፍ ዕቅድ መሠረት የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ለማድረግ የሚረዳ ግቦችና ኢላማዎችን በማስቀመጥና የድርጊት መርሃ ግብር የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍና በማዘጋጀት ወደ ትግበራ በመግባት በአገሪቱ ያለውን የህክምና መሣሪያዎች አቅርቦት ዕጥረት ሊቀርፍ እና አገሪቱ ለህክምና መሳሪያዎች ግዥ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ እንዲቀንስ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ሆስፒታሎች በእርዳታ የሚሰጡ የህክምና መሳሪያዎች ርክክብ ከመደረጉ በፊት በሆስፒታሎቹ የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ ወይም በሆስፒታሎች ማኔጅመንት እየተረጋገጠ ርክክብ

የሚደረግ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ሊከታተል ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆስፒታሎች መሳሪያዎቻቸውን በዓመቱ በእቅድ በመያዝ የደህንነት ፍተሻ (inspection and testing) እያስደረጉ ስለመሆኑ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሳሪያዎች በትክክል እየሰሩ ስለመሆኑ በየጊዜው የማረጋገጥ የመለካት (Calibration) ሥራ እየተሰራ ስለመሆኑ በአመታዊ እቅድ እየያዘ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአንድ የህክምና መሳሪያ ወደ ሌላ የህክምና መሳሪያ እንደመለዋወጫ መጠቀም የሚያስችል መመሪያ በቅድሚያ በማዘጋጀት ሆስፒታሎች እንዲጠቀሙበት በማሰራጨት ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተል ይገባል፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የጤና ሚኒስቴር በ1934 ዓ.ም በሀገር ግዛት ሚኒስቴር ሥር የህዝብ ጤና ጥበቃ ዴሬክሲዮን ተብሎ ተደራጀ፡፡ ከጊዜ በኋላ በ1940 ዓ.ም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተብሎ በአዋጅ ተቋቋመ፡፡ መስሪያ ቤቱ ከምስረታው ጀምሮ የንጉሱንና የመንግስታትን የጤና መመሪያዎች ሲያስፈጽምና ሲፈጽም ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ እስከ 1950ዎቹ ድረስ ኢትዮጵያ የምትመራበት ግልጽ የሆነና በይፋ የጸደቀ የጤና ፖሊሲ አልነበራትም፡፡

2. በንጉሰ ነገስቱ አገዛዝ ማለቂያ አካባቢ በዓለም የጤና ጥበቃ ድርጅት አነሳሽነት አጠቃላይ የጤና አገልግሎት ሥራዎች ሲሰሩ ነበር፡፡ በ1970ዎቹ አጋማሽ ላይ መንግስት በበሽታ መከላከልና መቆጣጠር ላይ ያተኮረ የዓለም ጤና ጥበቃ ያዘጋጀውን የሽልማት ዲክለሬሽን መሰረት አድርጎ ለመስራት ተንቀሳቅሷል፡፡

3. በ1986 ዓ.ም የዜጎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እንዲሁም የሀገሪቱን የወደፊት የልማት አቅጣጫ ግምት ውስጥ ያስገባ መከላከልን መሰረት ያደረገ የጤና ፖሊሲ ተቀረጸ፡፡ በዚህም መሰረት መንግስት ለጤና አገልግሎት መስፋፋት ልዩ ትኩረት በመስጠትና ህዝቡን በተደራጀ መልኩ ለማሳተፍ የዘርፉን ስራ ጀመረ፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለያዩ አዋጅ ቁጥሮች እና ስያሜዎች ሲጠራ ቆይቶ በአሁኑ ጊዜ የህብረተሰቡን ጤና በማስጠበቅ ጤናማና አምራች የሆነ ሕብረተሰብ ለመፍጠር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2013 መሠረት የጤና ሚኒስቴር በሚል ስያሜ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ

4. የፌዴራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2013 መሰረት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ራዕይ እና ተልዕኮ የሚከተሉት ናቸው፡፡

### ራዕይ

5. ጤናማ፣ ምርታማና የበለጸገ ኅብረተሰብ ተፈጥሮ ማየት፣

## ተልዕኮ

6. ጥራቱን የጠበቀ፤ ፍትሐዊና ተደራሽ የሆነ የጤና ማበልፀግ፣ በሽታ መከላከል፣ የፈውስ ህክምናና የተሃድሶ የጤና አገልግሎት በመስጠትና በመቆጣጠር የኢትዮጵያውያንን ጤናና ደህንነት ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ነው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

7. የፌዴራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2013 መሰረት ጤና ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣን፣ ኃላፊነትና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

- ጤናን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን ስትራቴጂዎች፣ ሕጎችን ይቀርጻል፣ ለአፈጻጸሙም ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሃ-ግብር ያዘጋጃል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- የጤናውን ዘርፍ ልማት ሀገራዊ ፕሮግራም ይነድፋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
- የጤና አገልግሎት ሽፋን ካርታ ያዘጋጃል፣ የጤና መሰረተ ልማቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
- የጤና አገልግሎት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ ያደርጋል፣ የጤና ፕሮግራሞችን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ የሀገሪቱን የጤና ችግር ለመፍታትና የጤና አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የሚረዱ ምርምሮች እንዲካሄዱ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤
- ሥርዐተ-ምግብ ሀገራዊ የአመጋገብ ሥርዓት ስትራቴጂ አፈፃፀምን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣
- ወረርሽን እና ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤
- የኅብረተሰቱን ጤና ሊጎዱ የሚችሉ ሁኔታዎችን የመከላከል እርምጃ ይወስዳል፣ ድንገተኛ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ የሌሎች አካላት ስራዎችን በማስተባበር ለችግሩ አፋጣኝና ውጤታማ መፍትሄ ይሰጣል፤
- አግባብነት ያላቸውን የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም የጤና አጠባበቅ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

- በሀገሪቱ ውስጥ የአስፈላጊ መድኃኒቶችና የሕክምና መሣሪዎች በቂ አቅርቦት መኖሩንና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
- የፌደራል ሆስፒታሎችን አስተዳደር በበላይነት ይቆጣጠራል፣ የፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች ማስተማሪያ ሆስፒታሎችን አቅም በማጎልበት ረገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ ይሠራል፤
- በሀገሪቱ ውስጥ የሚሰጠው የጤና ባለሙያዎች ሥልጠና ጥራትና አግባብነት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሰራል፣ ያረጋግጣል፤
- የምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና እንክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራዎች በአግባቡ መፈጸማቸውን ይከታተላል፤
- የባህል ህክምና ከዘመናዊው ህክምና ጋር እንዲቀናጅና አሠራሩን ከዘመናዊው መድኃኒት ጎን ለጎን እንዲሰራ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ይሰራል፤፤
- ሀገራዊ የጤና መድህን ሥርዓቱን ይመራል፤ አፈጻጸሙንም ይቆጣጠራል፤ ሀገራዊ የጤና መረጃ ሥርዓቱን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤፤
- በአዋጅ ቁጥር 276/1994 ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽህፈት ቤት የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን በሥራ ላይ ያውላል፤
- የጤና ባለሙያዎችን እና የጤና ተቋማትን በተመለከተ የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ይፈጽማል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡
- በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት እና ለጤና ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ጤና ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

የሚሉ ናቸው፡፡

## ለጤና ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት

8. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለጤና ሚኒስቴር ነው፡፡

፩/ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣

፪/ የኢትዮጵያ የደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት፣

፫/ አርማወርሐንሰን የምርምር ኢንስቲቲዩት፣

፬/ የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት፣

፭/ የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት፣

፮/ የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን፣

፯/ ቅዱስ ጴጥሮስ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣

፰/ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልና ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፣

፱/ አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣

፲/ አለርት አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣

፲፩/ የኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገልግሎት፤

፲፪/ የኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል፡፡

በተጨማሪ በፌዴራል መንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥር ያሉ ሆስፒታሎች በዩኒቨርሲቲዎቹ የሚተዳደሩና ዩኒቨርሲቲዎቹ ለትምህርት ሚኒስቴር፣ የጦር ሃይሎች ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝ ሆስፒታል ለመከላከያ ሚኒስቴር እና የፌዴራል ፖሊስ ሆስፒታል ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተጠሪ ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

9. በሚኒስትሮች ም/ቤት አዋጅ ቁጥር 1263/2014 የተሰጠውን ስልጣን፣ ኃላፊነትና ተግባራት ለመወጣት እንዲችል አንድ ሚኒስትር፣ ሶስት ሚኒስትር ዴኤታዎች በተጨማሪም 5 የፌደራል ሆስፒታሎች እና 7 ተቋማት በሚኒስትር መ/ቤቱ ስር ያገኛሉ፡፡ (ድርጅታዊ መዋቅሩ በአባሪ 1 ተያይዟል)

### የሰው ኃይል

10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ እስከ ሰኔ 30 ወር 2014 ዓ.ም 446 (49.6) ሴት ሠራተኞች 539 (50.4) ወንድ ሰራተኞች በድምሩ 985 ሠራተኞች ያሉት ሲሆን፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለው የሰው ሃይል በሙያ ሲተነተን ፒ.ኤች.ዲ 11፣ ማስተርስ 254፣ ዲግሪ 317፣ ዲፕሎማ እና ከዛ በታች ያሉ 403 ናቸው፡፡

11. ከዚህ ውስጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስር ለሚገኘው ለመድሀኒት፣ ሕክምና መሳሪያዎች እና መገልገያዎች የተመደበው የሰው ኃይል እስከ ጥር 2015 ዓ.ም ድረስ 5 ሴት ሠራተኞች

19 ወንድ ሰራተኞች በድምሩ 24 ሲሆን፤ ዳይሬክቶሬቱ ያለው የሰው ሃይል በሙያ ሲተነተን 15 ማስተርስ እና 9 ዲግሪ ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

12. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚኒስትሮች ም/ቤት በአዋጅ ቁጥር 1263/2013 የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለማስፈፀም ይረዳው ዘንድ ከመንግስት መደበኛ እና ካፒታል በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2012-2014 በጀት ዓመት ድረስ የተመደበለት መደበኛ እና ካፒታል በጀት እና አፈጻጸም በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

*ሀ. ለሚ/ር መ/ቤቱ ከመንግስት የተመደበ መደበኛ በጀት እና አፈጻጸም*

| በጀት አመት | የበጀት አይነት | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ስራ ላይ የዋለው በመብለጥ/በማነስ (በብር) | ሥራ ላይ የዋለ በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2012 | መደበኛ | 3,895,141,961.92 | 3,700,119,931.70 | 195,022,030.22 | 94.9% |
| 2013 | መደበኛ | 2,723,583,492.68 | 2,555,688,986.12 | 167,894,506.56 | 93.8% |
| 2014 | መደበኛ | 2,342,122,47.51 | 1,590,489,859.51 | -1,356,277,612 | 67.9% |

*ለ. ለሚ/ር መ/ቤቱ ከመንግስት የተመደበ ካፒታል በጀት እና አፈጻጸም*

| በጀት አመት | የበጀት አይነት | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ስራ ላይ የዋለው በመብለጥ/በማነስ (በብር) | ሥራ ላይ የዋለ በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2012 | ካፒታል | 921,096,403.91 | 764,896,858.57 | 156,199,545.34 | 83.0% |
| 2013 | ካፒታል | 1,044,328,618.71 | 616,192080.85 | 428,136,537.86 | 59% |
| 2014 | ካፒታል | 2,312,347,037.36 | 1,650,323,218.85 | 662,023,818.51 | 71.4% |

*በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመድሀኒት፣ሕክምና መሳሪያዎች እና መገልገያዎች የተመደበ መደበኛ እና ካፒታል በጀት እና አፈጻጸም*

| በጀት አመት | የበጀት አይነት | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ስራ ላይ የዋለው በመብለጥ/በማነስ (በብር) | ሥራ ላይ የዋለ በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2012 ዓ.ም | መደበኛ | - | - | - | - |
| | ካፒታል | **370,000** | **0** | **370,000** | **0%** |
| | **ድምር** | **370,000** | **0** | **370,000** | **0%** |
| 2013 ዓ.ም | መደበኛ | 4,041,300 | 3,868,475.74 | 172,824.26 | 96% |
| | ካፒታል | 268,000 | 0 | 268,000 | 0% |
| | **ድምር** | **4,068,100** | **3,868,475.74** | **199,624.26** | **95%** |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 2014 ዓ.ም | መደበኛ | 5,450,000 | 2,453,083.2 | 2,996,916.8 | 45% |
| | ካፒታል | 6,664,800 | 5,258,388.38 | 1,406,411.62 | 79% |
| | **ድምር** | **12,114,800** | **7,711,471.58** | **4,403,328** | **64%** |

## የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ

13. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በፌዴራል ሆስፒታሎች (ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆኑትና ያልሆኑትን ጭምር) የህክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ያሉ ችግሮች እንዲለዩ እና የተለዩት ችግሮች የሚፈቱበት ስልት እንዲነደፍ የማድረግ ሥራዎች ቀልጣፋ መሆናቸውን፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ስለህክምና መሳሪያዎች ያወጣቸው ደረጃዎች(ስታንዳርዶች) በትክክል ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ክትትል እና ድጋፍ ማድረጉን እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን ሲሆን፤ይህን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦች ማቅረብ ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)

14. በፌዴራል ሆስፒታሎች የህክምና መሣሪያዎች አገልግሎት ለመስጠት የተዘረጋው የአሰራር ስርዓት እና አፈጻጸም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

15. ከላይ ለተጠቀሰው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሶስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም፡-

1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽ፣ ጥራቱን የጠበቀና ቀልጣፋ እንዲሆን የአሰራሩ ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፣
2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሣሪያዎች በአግባቡ እየሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣
3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በህክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ከሆስፒታሎች እና ሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ያለው የመረጃ ልውውጥ እና ቅንጅታዊ አሰራር ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣

የሚሉ ናቸው፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

16. ከላይ የተቀመጡትን የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 23 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የፌዴራል ሆስፒታሎች የሕክምና መሳሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀምን የሚመለከቱ መቋቋሚያ አዋጅ፣ የየዓመቱ ዕቅድ እና ዕቅድ አፈፃፀሞችን (ከ2012-2014 ዓ/ም)፣ የማኔጅመንት ቃለ-ጉባኤዎችን (ከ2012 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም) ፣ የጤና ፖሊሲ (መስከረም 1986 ዓ.ም)፣ ሁለተኛው የጤናው ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2013 ዓ.ም - 2017 ዓ.ም) (2020/21-2024/25) እና የአስር ዓመት የጤና እቅድን ከ2013 ዓ.ም እስከ 2022 ዓ.ም እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡
17. የተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተልከው በኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹ (በአባሪ 2 ) ተያይዘዋል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

18. የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፉ የዋና ኦዲተሮች መ/ቤት ማህበር (INTOSAI) የተዘጋጀውን አለም-አቀፍ የክዋኔ ኦዲት ስታንዳርድ (ISSAI) መሰረት እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2012 ጀምሮ ዝርዝር ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ታህሳስ ወር 2015 በጀት ዓመት ሁለተኛ ሩብ ዓመት ድረስ ያሉትን የሥራ ክንውኖች ነው፡፡ ኦዲቱ በዋኛነት ያተኮረው በፌዴራል ሆስፒታሎች የሕክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ነው፡፡
19. ኦዲቱ የተከናወነው በጤና ሚኒስቴር ዋና መ/ቤት ነው፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል ሆስፒታሎች የሕክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ የአሰራር ሥርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ በናሙና ለተመረጡ የፌዴራል ሆስፒታሎች እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና በመላክ እና ተጠይቀው የቀረቡ ማስረጃዎችን በመከለስ ነው፡፡ መጠይቅ የቀረበላቸውና የተላከላቸው የፌዴራል ተቋማት ዝርዝር (በአባሪ 3 ) ተያይዘዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ፖሊሲ፣ መመሪያ እና ስትራቴጂ ማዘጋጀትን በተመለከተ፣

20. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገር አቀፍ የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ፖሊሲ፣ መመሪያ እና ስትራቴጂ አዘጋጅቶ በማፀደቅ ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሰራጭ እና ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

21. በኦዲቱ ወቅት አገር አቀፍ የጤና ፖሊሲ ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሆስፒታል አገልግሎት ማሻሻያ መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን አገር አቀፍ የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደርን በሚመለከት ራሱን የቻለ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና መመሪያ ያላዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

22. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ለተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Factsheet) በፅሁፍ በሰጡት መልስ እና ለተላከላቸው ረቂቅ ሪፖርት በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ከዚህ በፊት ፖሊሲ፣ መመሪያና ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ እንደነበር፤ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ጀምሮ ግን ማንኛውም መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር መዘጋጀት እንዳለበት በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደተላከ በቅድሚያ ግን ፖሊሲ ይፅደቅ በተባለው መሰረት ረቂቁ መዘጋጀቱን ገልፀዋል፡፡

23. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ ፍትህ ሚኒስቴር በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተዘጋጅተው የጸደቁትን መመሪያዎች የመመዝገብና ለተቋማት በዝግጅት ወቅት የመደገፍ ኃላፊነት እንጂ መመሪያ ማዘጋጀት ኃላፊነቱ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በመሆኑ፣ ፖሊሲ፣ መመሪያና ስትራቴጂ በፍትህ ሚኒስቴር በኩል እንዲዘጋጅ አቅጣጫ የተሰጠበት እና ተዘጋጀ የተባለው ረቂቅ ፖሊሲ እንዲቀርብ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

24. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደርን የሚመለከቱ ፖሊሲ፣ መመሪያዎችና ስትራቴጂዎችን አዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቁ በማድረግ ሆስፒታሎች እንዲጠቀሙባቸው አለማሰራጨቱ በህክምና መሳሪያዎች

አጠቃቀም ላይ የተዘበራረቁ አሰራሮች እንዲኖሩ ሊያደርግ ከመቻሉም በላይ ያሉ ችግሮች በወቅቱ እንዳይፈቱ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

**የሕክምና መሳሪያዎች ግዥን በተመለከተ፤**

25. የህክምና መሳሪያዎችን የግዥ ፍላጎት ከሚመለከታቸው አካላት በመሰብሰብ እና በአመታዊ የግዥ ዕቅድ ውስጥ በማካተት ግዥው ሊፈጸም ይገባል፡፡

26. ይሁን እንጂ በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው የታዩት ሁሉም ሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያ ፍላጎታቸውን በቅድሚያ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠይቀው የማያውቁ መሆኑ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱም በየዓመቱ የሆስፒታሎችን የህክምና መሳሪያዎች ፍላጎትን መሰረት በማድረግ ግዥ የማያከናውን መሆኑ ታውቋል፡፡

27. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Factsheet) በፅሁፍ በሰጡት መልስ እና ለተላከላቸው ረቂቅ ሪፖርት በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከመ/ቤቱ ስትራቴጂክ እቅዶች፣ አዲስ ከሚገነቡ የጤና ተቋማትና አገልግሎት ማስፋፊያዎች፣ በሆስፒታሎች በሚደረግ የመስክ ምልከታ፤ ከሆስፒታሎች በሚመጣ የድጋፍ ጥያቄ እና ከ(MEMIS) ሶፍትዌር አማካይነት በሚገኝ መረጃ መሰረት የግዥ ፍላጎት እንደሚለይ ገልፀዋል፡፡

28. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየዓመቱ የሆስፒታሎችን የህክምና መሳሪያዎች ፍላጎትን መሰረት በማድረግ የግዥ ፍላጎት ዕቅድ እና በዕቅዱም መሠረት ግዥ ስለመፈጸማቸው የሚያሳዩ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልቀረቡ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

29. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሆስፒታሎችን የሕክምና መሳሪያዎች በቅድሚያ በመጠየቅ በሚኒስቴር መ/ቤቱ አመታዊ እቅድ ውስጥ እየተያዙ ተገዝተው እንዲከፋፈሉ ባለመደረጉ ሆስፒታሎች በህክምና መሳሪያዎች እጥረት ሥራቸው እንዲስተጓጎል ከማድረጉም በላይ መንግስት ከጥቅል ግዥ የሚያገኘውን ጠቀሜታ ሊያሳጣው ይችላል፡፡

## የህክምና መሳሪያዎች ስፔስፊኬሽን ዝግጅት በተመለከተ፤

30. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመንግስት የጤና ተቋማት የህክምና መሳሪያዎች ግዥ ለመፈፀም የሚያስችል ስፔስፊኬሽን ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር በማዘጋጀት ግዥውም በስፔስፊኬሹ መሠረት መፈጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

31. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመንግስት የጤና ተቋማት የህክምና መሳሪያዎች ግዥ ለመፈፀም የሚያስችል ስፔስፊኬሽን ያላዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

32. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ ሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎች ግዥ ለመፈፀም የሚያስችል ወጥ የሆነ ስፔስፊኬሽን ባለመኖሩ ትክክለኛውን የመሳሪያ ዓይነት በመምረጥ መግዛት እንዳይቻል በማድረጉ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ በሚውሉበት ወቅት የጥራት ችግር እንደሚያጋጥማቸው ገልፀዋል፡፡

33. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ለተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Factsheet በፅሁፍ በሰጡት መልስ እና ለተላከላቸው ረቂቅ ሪፖርት በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመንግስት የጤና ተቋማት የህክምና መሳሪያዎች ግዥ ለመፈፀም የሚያስችል ስፔስፊኬሽን አዘጋጅቶ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ድረ-ገፅ/Web-site ላይ በመጫን ለሆስፒታሎች ተደራሽ ለማድረግ የተቻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

34. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ ድረ-ገፁ ላይ ለማረጋገጥ ጥረት የተደረገ ቢሆንም ለማግኘት ያልተቻለ በመሆኑ የተሰጠውም ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

35. ለሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎች ግዥ ለመፈፀም የሚያስችል ስፔስፊኬሽን በቅድሚያ በሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በማካተት ተዘጋጅቶ ግዥ እንዲፈጸም አለመደረጉ ሆስፒታሎች በመሳሪያዎች ግዢ ላይ የሚያጋጥሟቸውን የጥራት ችግሮች መፍታት እንዳይችሉ እና የተገዛው የህክምና መሳሪያ ለታለመለት ሥራ እንዳይውል ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የህክምና መሳሪያዎች ግዥ ለጠየቁት አካላት የደረሱ ስለመሆኑ፣

36. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የህክምና መሳሪያዎች ግዥ ከተፈጸመ በኋላ ለጠየቁት አካላት መድረሱ የሚረጋገጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

37. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆስፒታሎች እንዲገዛላቸው የጠየቋቸው የህክምና መሳሪያዎች በጠየቁት እና አስቀድሞ በተዘጋጀው ስፔስፊኬሽን መሆኑ እየተረጋገጠ በትክክል

የደረሳቸው መሆኑን የሚረጋግጥበት ሥርዓት ያልዘረጋ እና ከ2012-2014 ባሉት ዓመታት የስንት የሕክምና መሣሪያዎች ግዥ እና ለእነማን ግዥው እንደተፈጸመ፣ የተገዙትም ለጤና ተቋማት (ሆስፒታሎች) የተላኩት የህክምና መሳሪያዎች ስለመድረሳቸው የሚያሳዩ ማስረጃዎች ያልቀረቡ ከመሆኑም በላይ ክትትል ስለመደረጉ የሚያሳዩ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም፡፡

38. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ፣ለተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Factsheet በፅሁፍ በሰጡት መልስ እና ለተላከላቸው ረቂቅ ሪፖርት በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ የህክምና መሳሪያዎች ግዥ ለጠየቁት አካላት መድረሱን በተመለከተ መሳሪያው የተላከላቸው ጤና ተቋማት (ሆስፒታሎች) ስለመድረሱ የሚገልፅ ማስረጃ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደሚልኩ፤ በተጨማሪም የክልል ጤና ቢሮዎች እንደአስፈላጊነቱ መረጃ እንደሚልኩ ገልፀዋል፡፡

39. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለፉት አመታት የህክምና መሳሪያዎችን ገዝቶ ለተላከላቸው ተቋማት (ሆስፒታሎች) የደረሰ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲቀርብ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

40. በሚኒስቴር መ/ቤቱ አማካይነት ለሆስፒታሎች ተገዝተው የተላኩ የህክምና መሳሪያዎች በትክክል መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ የተገዛው የህክምና መሳሪያ ለታለመለት ዓላማ እንዳይውል ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን በቅንጅት መገልገልን በተመለከተ፤

41. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመንግስት ሥር ባሉ ሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን በቅንጅት አገልግሎት መስጠት የሚችሉበትን አሠራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

42. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል መንግስት ሥር ባሉ ሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን በቅንጅት አገልግሎት መስጠት የሚችሉበትን አሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

43. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህን ተግባር ለማከናወን በ2015 ዓ.ም እቅዱ ላይ እንዲካተት አድርጎ እንደነበር፣ ነገር ግን በሂደት መ/ቤቱ ሆስፒታሎች ካለባቸው ጫና አንፃር አዋጭ አለመሆኑን በመገንዘቡ አለማከናወኑን ገልፀዋል፡፡

44. በተጨማሪም ለተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Factsheet) እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በፅሁፍ በሰጡት መልስ በህክምና መሳሪያዎች ላይ ስራውን ለማስፋት እየተሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

45. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ ይህን ተግባር ማከናወን የማይቻል መሆኑ የተረጋገጠበት የአዋጭነት ጥናት እና አሰራሩን ለማስፋት እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችን የሚየሳዩ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸውና ቢያንስ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ በሆኑ ተቋማት የሚገኙ የሕክምና መሣሪያዎች በጋራ ለመጠቀም የሚያስችል አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይቻል የነበረ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

46. የመንግስት ሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎችን በቅንጅት አገልግሎት መስጠት የሚችሉበትን አሰራር አለማመቻቸት በተወሰኑ ሆስፒታሎች ብቻ ጫና እንዲኖር የሚያደርግ እና ተገልጋዮችን ለተጨማሪ ወጪና እንግልት ሊዳርግ ይችላል፡፡

## የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ማድረግን በተመለከተ፣

47. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

48. በአገሪቱ የ10 ዓመት (2013- 2022) የልማት ዕቅድ ከተጠቀሱት የጤና ልማትን በሚመለከት ትኩረት ከሚያስፈልጋቸው መካከል የህክምና መገልገያ መሣሪያዎችን በአስተማማኝ ሁኔታ ማቅረብ አንዱ መሆኑ የተገለጸና ይህን ለማስፈጸም ከተቀመጡት ስልቶች ውስጥ የግሉን ዘርፍ የህክምና መገልገያ ቁሳቁሶችን እንዲያመርት ማድረግ መሆኑ ተቀምጧል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጀው የ10 ዓመት የጤና ዘርፍ ዕቅድ ላይ በአገር ውስጥ የህክምና መሣሪያዎችን እንዲመረቱ ለማሳደግ ስትራቴጂ ነድፎ እንደሚገባ እና የህክምና መሣሪያዎችን በአገር ውስጥ ማምረት ከግሉ ዘርፍ ከሚጠበቁ ተሳትፎዎች አንዱ መሆኑ ተቀምጧል፡፡

49. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ከውጭ የሚመጣውን ለመቀነስ እና በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ለማድረግ ስትራቴጂ ያልነደፈ መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በጤና ዘርፍ የ10 ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ላይ ከተቀመጡ 28 ኢላማዎች ውስጥ የህክምና መሣሪያዎችን በአገር ውስጥ ማምረት እና የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ የሚመለከቱ ኢላማዎች የሌሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

50. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ይህ ተግባር የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊነት አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

51. በተጨማሪም ለተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Factsheet) እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በፅሁፍ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የአስር ዓመት ስትራቴጂ (ከ2013-2022) ነድፎ በመተግበር ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

52. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ ጤናን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን ስትራቴጂዎች፣ ሕጎችን መቅረጽ፣ ለአፈጻጸሙም ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሃ-ግብር ማዘጋጀት፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ማድረግ ሃላፊነትና የጤና ዘርፉን የሚመለከቱ ጉዳዮች በበላይነት የመመራትና የማስተባበር የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊነት በመሆኑ እንዲሁም ስትራቴጂ ነድፎ እየሰራ ስለመሆኑ ምላሽ ቢሰጥም ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

53. የሕክምና መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ አለማድረግ መሳሪያዎች አቅርቦት ላይ የሚገጥሙ ችግሮች በአፋጣኝ እንዳይፈቱ ከማድረጉ በተጨማሪ በአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ወጪ ለመቀነስ የተቀመጠው ጥረት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

**በየሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎችን ሁኔታ የሚከታተል የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ መኖሩን በተመለከተ፤**

54. በሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎችን ሁኔታ የሚከታተል የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ (Medical Equipment Management Committee/MEMC) ሊቋቋም እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም መቋቋማቸውን የሚከታተልበት ስርዓት ዘርግቶ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

55. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- በናሙና የታዩ ሁሉም የፌዴራል መንግስት ሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎችን ሁኔታ የሚከታተል የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ (Medical Equipment Management Committee/MEMC) ማቋቋማቸውን ቢገልፁም ስለመቋቋሙ የሚያሳዩ ማስረጃዎች እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ያላቀረቡ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱም በሁሉም ሆስፒታሎች ኮሚቴው ስለመቋቋሙ እና ስራ እየሰሩ ስለመሆኑ ክትትል ያደረገበት ማስረጃ እንዲያቀርብ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያላቀረበ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

56. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው እና ለተላከለት ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Factsheet) እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ በፅሁፍ በሰጡት መልስ ሆስፒታሎች በHospital service transformational guideline ላይ ኮሚቴ መቋቋም እንዳለበት ስለተጠቀሰ ማቋቋም እንዳለባቸው፣ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህንን የሚከታተል ባለሙያ እንደነበረው ገልፀዋል፡፡

57. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ ከላይ በተጠቀሰው ሰነድ ላይ ኮሚቴው ማሟላት ያለበትን ቅድመ ሁኔታዎች በማሟላት የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ (Medical Equipment Management Committee/MEMC) አቋቁመው እየሰሩ መሆናቸውን ክትትል ያደረገበት ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

58. የህክምና መሳሪያዎችን አስተዳደር ኮሚቴ አለመቋቋሙ በመሳሪያዎች ዙሪያ በሰነዱ ላይ የተጠቀሱ ኮሚቴውን የሚመለከቱ ሃላፊነቶች በአግባቡ እንዳይከናወኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## በእርዳታ የሚገቡ የህክምና መሳሪያዎች ርክክብ ከመደረጉ በፊት በህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ መረጋገጡን በተመለከተ፣

59. ለፌዴራል ሆስፒታሎች በእርዳታ የሚገቡ የህክምና መሳሪያዎች ርክክብ ከመደረጉ በፊት (የተላከው መሳሪያ ብዛት፣ ስለመስራት አለመስራታቸው ወዘተ) በህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ ወይም በሆስፒታሎች ማኔጅመንት ሊረጋገጡና

ምዝገባም ሊካሄድላቸው ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህ ተግባራዊ መደረጉን የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

60. ይሁን እንጂ በእርዳታ የሚገቡ የህክምና መሳሪያዎች ርክክብ ከመደረጉ በፊት በማረጋገጥ ርክክብ የሚያደርግ ኮሚቴ አለመኖሩ በናሙና ተመርጠው የታዩ ሆስፒታሎች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

61. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ሆስፒታሎች በእርዳታ የሚገቡ የህክምና መሳሪያዎች ርክክብ ከመደረጉ በፊት በህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ ወይም በሆስፒታሎች ማኔጅመንት እየተረጋገጠ ርክክብ የሚደረግና የሚመዘገቡ ስለመሆኑ የሚከታተልበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

62. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ለሆስፒታሎች በእርዳታ የሚገቡ የህክምና መሳሪያዎች ርክክብ ከመደረጉ በፊት በህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ ወይም በሆስፒታሎች ማኔጅመንት መረጋገጣቸውን ክትትል ማድረግ የማይጠበቅበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

63. በተጨማሪም ለተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Factsheet) እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በፅሁፍ በሰጡት መልስ በእርዳታ የሚገባው መሳሪያ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የተገኘ ከሆነ የመድሃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ መሳሪያውን በሚያደርስበት ወቅት ከተጠቃሚው ጤና ተቋም መሳሪያው ስለመድረሱ የሚገልፅ ሞዴል 19 በማስቆረጥ ሪፖርት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደሚልክ፤መሳሪያው ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ውጪ በሆስፒታሎች ጥረት የተገኘ ከሆነ ርክክቡ በጤና ተቋማት ማኔጅመንት በኩል እንደሚከናወንና በዚህ ዙሪያ ክፍተቶች ሲገኙ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እርምጃ እንደሚወስድ ገልፀዋል፡፡

64. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ ሚ/ር መ/ቤቱ በተቋቋመበት አዋጅ ቁ.1236/2013 መሰረት በሀገሪቱ ህዝብ ስም በዕርዳታ የሚመጡት የሕክምና መሣሪዎች ትክክለኛው ርክክብና ምዝገባ መደረጉንና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ስላለበት እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ርክክብ የተደረገባቸው እና ለጤና ተቋማት ያስረከበባቸው ሰነዶች እንዲሁም በሆስፒታሎች በራሳቸው ጥረት የተደረጉ መሳሪያዎች ርክክብ ላይ ክትትል ተደርጎ የተከሰቱ ክፍተቶች ላይ የተወሰዱ እርምጃዎች ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

65. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ሆስፒታሎች በእርዳታ የሚገቡ የህክምና መሳሪያዎች ርክክብ በሚመለከታቸው አካላት ርክክብ መደረጉን መመዝገባቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት አለመኖሩ በህክምና መሳሪያዎች ዙሪያ የሚከሰቱ የጥራት፣ የብልሽት፣ የግዥ መዘግየት እና የመሳሰሉት ችግሮች በወቅቱ ምላሽ እንዳያገኙ፣ መሳሪያዎች ለሚመለከታቸው የጤና ተቋማት መድረሳቸውን ማረጋገጥን እንዳይቻልና ከታለመላቸው ዓላማ ውጪ እንዲውሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**በየሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሳሪያዎች በመደበኛነት የደህንነት ፍተሻ እየተደረገላቸው መሆኑ በተመለከተ፤**

66. በየሆስፒታሎች በሥራ ላይ ያሉ ህክምና መሳሪያዎች መደበኛ የፍተሻ በአመታዊ እቅድ በመያዝ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ በባለሙያ የደህንነት ፍተሻ (inspection and testing) ሊደረግላቸው እና የመሣሪያ አምራቹ በሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ መሠረት ትክክለኛነታቸው (Calibration) ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

67. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች በሥራ ላይ ያሉ ህክምና መሳሪያዎች በአመታዊ ዕቅድ ተይዞ መደበኛ የፍተሻ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ባለሙያ የደህንነት ፍተሻ (inspection and testing) እና መሣሪያዎቹ ትክክለኛነታቸው (Calibration) እያስደረጉ ስለመሆኑ ክትትል የሚያደርግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

68. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በሆስፒታሎች በስራ ላይ ያሉ ህክምና መሳሪያዎች መደበኛ የፍተሻ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ በሚመለከታቸው በባለሙያዎች የደህንነት ፍተሻ እና የመለካት ስራ እየተሰራ መሆን አለመሆኑን ክትትል የማድረግ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

69. በተጨማሪም ለተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Factsheet) እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በፅሁፍ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተመረጡ የጤና ተቋማት በሚያከናውናቸው ድጋፋዊ ጉብኝቶች ምልከታዎችን በማድረግ እንደሚከታተል ገልፀዋል፡፡

70. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ ሚ/ር መ/ቤቱ በተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 1263/2013 ላይ በሀገሪቱ ውስጥ የአስፈላጊ የሕክምና መሣሪያዎች ትክክለኛነታቸውና ደህንነታቸው ተረጋግጦ በአግባቡ ጥቅም ላይ

መዋላቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ስላለበት፤ እንዲሁም ክትትል ስለመደረጉ እና የተሰጠውን ግብረመልስ የሚያሳዩ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

71. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሆስፒታሎች በመደበኛነት የህክምና መሳሪያዎቻቸውን የደህንነት ፍተሻና ካሊብሬሽን እያደረጉ መሆን አለመሆናቸውን አለማረጋገጥ በመሳሪያዎች አማካኝነት ተመስርቶ የሚደረግ ምርመራ ውጤት ላይ እና የተቋማቱ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

## የሕክምና መሳሪያዎች የሚጠገኑበት ማዕከልን በተመለከተ፤

72. በመንግስት ሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሣሪያዎች ሲበላሹ የሚጠገኑበት የተደራጀ የህክምና መሣሪያዎች ማዕከል ሊቋቋም ይገባል፡፡

73. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ሁሉም የመንግስት ሆስፒታሎች፡-

- የሚገኙ የህክምና መሣሪያዎች ሲበላሹ የሚጠገኑበት የተደራጀ የህክምና መሣሪያዎች ማዕከል ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- በፌደራል መንግስት ሥር ባሉ ሆስፒታሎች ውስጥ ከአንድ የህክምና መሳሪያ አካል ወደ ሌላ የህክምና መሳሪያ በመውሰድ እንደመለዋወጫ መጠቀም የሚያስችል መመሪያ ሳይዘጋጅ እና ስርዓት ሳይዘረጋ ከአንድ መሳሪያ ዕቃ ወስዶ ለሌላ መሳሪያ የሚገጠም መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

74. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ለተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Factsheet) እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በፅሁፍ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች የሚገኙ የጥገና ማዕከላት የተደራጁ እንዲሆኑ እየሰራ እንደሚገኝ፤ መለዋወጫን ከአንዱ መሳሪያ ወደ ሌላ መሳሪያ መጠቀምን በተመለከተ መመሪያ እንደሌለ ነገር ግን ሁለት ተመሳሳይ መሳሪያ ላይ ከአንዱ ወደ ሌላው መጠቀም የሚያስችል ድራፍት ማንዋል መዘጋጀቱን ገልፀዋል፡፡

75. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ በሆስፒታሎች የሚገኙ የጥገና ማዕከላት የተደራጁ እንዲሆኑ እየሰራ መሆኑን እና ከአንድ መሳሪያ ወደ ሌላ መሳሪያ መጠቀምን በተመለከተ እንደተዘጋጀ የተገለፀው ማንዋል በኦዲቱ

ወቅት ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

76. ሆስፒታሎች የተደራጀ የህክምና መሳሪያዎች ጥገና ማዕከል አለመኖሩ የተበላሹ መሳሪያዎች በወቅት ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዳይችሉ፣ ከአንድ መሳሪያ ወደ ሌላ መሳሪያ ያለ መመሪያ የሚደረገው ልውውጥ ደግሞ ለስርቆትና ለመጥፋት መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

## የሕክምና መሳሪያዎች አወጋገድ መመሪያን በተመለከተ፣

77. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎችን ለማስወገድ የሚረዳ ማንዋል ወይም መመሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በማዘጋጀትና ለሚመለከታቸው ፈጻሚ አካላት በማሰራጨት ተግባራዊ መደረጉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተወገዱ የህክምና መሳሪያዎች ከኢንቨንተሪ ዝርዝር ላይ የተሰረዙ መሆናቸውን የሚረጋግጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

78. በኦዲቱ ወቅት በኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ባለስልጣን የህክምና መሳሪያዎች አወጋገድ መመሪያ (Medical Device Decommissioning and Disposal Guideine) ተዘጋጅቷል፡፡ ይሁን እንጂ

- የፌደራል መንግስት ባወጣው የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት በናሙና ተመርጠው የታዩ ሁሉም ሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎችን አስወግደው ስለማያውቁ የማያገለግሉ የህክምና መሳሪያዎችን (ንብረቶችን) ከኢንቨንተሪ የመሰረዝ ስራ ያላከናወኑ መሆኑ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ተግባራዊ ማድረጋቸውን ያልተከታተለ መሆኑ፣
- በኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ባለስልጣን ባዘጋጀው መመሪያ ላይ የሚወገዱ የህክምና መሳሪያዎች እስኪወገዱ ድረስ ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ መቀመጥ እንዳለበት እንዲሁም መወገድ ያለባቸው መሳሪያዎች ከአንድ ዓመት በላይ ሳይወገዱ መቆየት እንደሌለባቸው የተጠቀሰ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህን መመሪያ ሆስፒታሎች ተግባራዊ እንዲያደርጉት ያላደረገ መሆኑና መመሪያውን እንደማያውቁት መግለጻቸው፣

ታውቋል፡፡

79. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ 8 የፌዴራል ሆስፒታሎች (ሦስት ለጤና ሚኒስቴር ተጠሪ ሆኑ፣ ሦስት የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች፣ የመከላከያ እና እና የፌዴራል ፖሊስ ሆስፒታሎች) ውስጥ፡-

- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ሆስፒታሉ ባዘጋጀው መመሪያ መሰረት መሳሪያዎችን እንደሚያስወግድ የተገለጸ ቢሆንም የተዘጋጀው መመሪያ እንዲቀርብ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣.
- አለርት አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የኢንፎርሜሽን ሲስተሙን በማጥፋት፣ የሲሪያል እና ሞዴል ቁጥሮችን በማስወገድ ወደ አሮጌ ወይም የማይሰሩ መሳሪያዎች ማከማቻ በሚቀመጡበት ስቶር እንዲቀመጡ ማድረግ ብቻ እንጂ አስወግዶ የማያውቅ መሆኑ፣
- በመከላከያ ሚኒስቴር የጦር ሃይሎች ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝ ሆስፒታል የህክምና መሳሪያዎችን ኮሚቴ በማቋቋም ያለመመሪያ እንደሚያስወግድ፣ በመለዋወጫ ችግር አገልግሎት የማይሰጡ የህክምና መሳሪያዎችን ወይም የባዬሜዲካል ባለሙያዎች አይሰራም ካሉ በኋላ ቦዲያቸውን በማውጣት ለሌላ የህክምና መሳሪያ መለዋወጫ የሚጠቀሙበት (Canibalised) መሆኑ፣
- ቀሪዎቹ አምስቱ (ቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል፣ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል፣ ፌዴራል ፖሊስ ጤና አገልግሎት፣ የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና የጅማ ዩኒቨርሲቲ ህክምና ማዕከል) ምንም የህክምና መሳሪያዎች አወጋገድ መመሪያ የሌላቸው እና አስወግደው የማያውቁ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

80. በተጨማሪም ከአንድ የህክምና መሳሪያ ወደ ሌላ የህክምና መሳሪያ በመውሰድ እንደመለዋወጫ መጠቀም የሚያስችል መመሪያ በቅድሚያ ሳይዘጋጅ ሆስፒታሎች ከአንድ መሳሪያ እቃ ወስደው ወደ ሌላ መሳሪያ የሚገጠሙ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ሆስፒታሎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

81. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ለተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Factsheet) በፅሁፍ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጀው የሆስፒታል አገልግሎት ማሻሻያ መመሪያ ሰነድ ውስጥ መሳሪያዎች አገልግሎት ጊዜያቸው ሲያበቃ እንዴት መወገድ እንዳለባቸው አቅጣጫ የተቀመጠና ሰነዱም ለተቋማቱ ተደራሽ መደረጉን ገልፀዋል፡፡

82. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡-

- በናሙና የታዩ ሆስፒታሎች ያስወገዱት ንብረት የሌለ በመሆኑ፣
- በመንግስት የንብረት አወጋገድ መመሪያ ላይ ሆነ የሆስፒታል አገልግሎት ማሻሻያ መመሪያ ላይ ከተጠቀሱት ንብረት የማስወገጃ ዘዴዎች ውስጥ ከአንዱ መሣሪያ ላይ አንድ ክፍል ወስዶ ሌላውን መጠገን (Canibalised) ማድረግን ባለመጠቀሱ፣
- በኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ባለስልጣን በተዘጋጀው የህክምና መሳሪያዎች አወጋገድ መመሪያ መሰረት የሚወገዱ የህክምና መሳሪያዎች ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ያልተቀመጡ ከአንድ ዓመት በላይ ሳይወገዱ የቆዩ በመሆኑ፣

የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

83. የማያገለግሉና መወገድ ያለባቸው የህክምና መሳሪያዎች በወቅቱ ባለመወገዳቸውና ከመዝገብ አለመሰረዛቸው፣ ያለመመሪያ ከመሣሪያዎች አካል ላይ ለመለዋወጫ በማለት መነቃቀል ለህገ-ወጥ አሠራር በር የሚከፍት፣ የተበላሹ መሣሪያዎች በምትካቸው ሌላ የህክምና መሳሪያ እንዳይተካ ምክንያት ከመሆኑም በላይ ሆስፒታሎችን ለቦታ ጥበት እና አገልግሎታቸውን በማስፋፋት ዙሪያ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡


## የሚወገዱ የህክምና መሳሪያዎች ተለይተው የሚቀመጡበት ቦታን በተመለከተ፤

84. ከየሆስፒታሎች የሚወገዱ የህክምና መሳሪያዎች ተለይተው ሊቀመጡ ይገባል፡፡

85. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ፡

- መወገድ ያለባቸው መሳሪያዎች አገልግሎት ከሚሰጡ እቃዎች ጋር በአንድ ክፍል/መጋዘን ውስጥ በጋራ እና በየሆስፒታሎች ኮሪደርና ግቢ ውስጥ ያለመጠለያና ጥበቃ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣
- በሁሉም ሆስፒታሎች መወገድ ያለባቸው የህክምና መሳሪያዎች ተለይተው የሚቀመጡበት ቦታ አለመኖሩ፤

በአካል ከተደረገ ጉብኝት ለመረዳት ተችሏል፡፡



**በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል መወገድ ያለባቸው ነገር ግን በየኮሪደሩ ተቀምጠው የሚገኙ የህክምና መሳሪያዎች**

86. መወገድ ያለባቸው መሳሪያዎች አገልግሎት ከሚሰጡ መሳሪያዎች ጋር በጋራ በመቀመጣቸው ምክንያት የቦታ ጥበት እንዲፈጠር በማድረጉ የሆስፒታሎቹ

አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ችግር መፍጠሩን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ ሆስፒታሎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

87. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በበጀትና ቦታ ችግር ምክንያት በየሆስፒታሉ የሚገኙ መወገድ ያለባቸው መሳሪያዎች ተለይተው እንዲቀመጡ ማድረግ አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

88. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ በየሆስፒታሎች የሚገኙ መወገድ የሚገባቸው መሳሪያዎች የኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ባለስልጣን ባዘጋጀው የህክምና መሳሪያዎች አወጋገድ መመሪያ መሰረት እንዲወገዱ የተለዩ መሳሪያዎች ከአንድ ዓመት በላይ መቆየት እንደሌለባቸው በመመሪያው ተገልፃል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይህን ተግባር ሆስፒታሎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ መመሪያውን በማሰራጨት ተግባራዊ መደረጉን ክትትልና ድጋፍ ባለማድረጉ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

89. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መወገድ የሚገባቸውን የህክምና መሳሪያዎች አካባቢን ሊበክሉ በማይችሉበት ሁኔታ በባለሙያ ተለይተው ለብቻቸው አለመቀመጣቸው ለአካባቢ ብክለት፣ለስርቆት ሊጋለጥ እና የቦታ ጥበት እንዲከሰት ሊያደርግ ይችላል፡፡

## በየሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሳሪያዎች ያሉበት ወቅታዊ ሁኔታ መረጃ መያዝን በተመለከተ፤

90. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሳሪያዎች ያሉበት ወቅታዊ ሁኔታ (በስራ ላይ ስለመሆን አለመሆናቸው፣ ጥገና የሚያስፈልግ ስለመሆኑ ወዘተ) የሚከታተልበት፣ መረጃ የሚይዝበትና ልውውጥ የሚደረግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

91. ይሁን እንጂ በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩ ስምንት የፌዴራል ሆስፒታሎች ውስጥ፡-

- አራቱ (ቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል፣ አለርት ሆስፒታል፣ ቅዱስ ጳውሎስ እና የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝ ሆስፒታል) ከሚ/ር መ/ቤቱ ጋር የህክምና መሳሪያዎች ያሉበት ወቅታዊ ሁኔታ መረጃዎችን የሚለዋወጡ እንደሆነ ቢገልፁም ማስረጃ ያላቀረቡና በሚኒስቴር መ/ቤቱም ያልቀረበ መሆኑ፣

➢ ቀሪዎቹ አራት ሆስፒታሎች (የጥቁር አንበሳ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል፣ የጦር ሀይሎች ኮምፕርሂንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የፌዴራል ፖሊስ ጤና አገልግሎት ዋና መምሪያ እና ጅማ ዩኒቨርስቲ ህክምና ማዕከል) የህክምና መሳሪያዎች ያሉበት ወቅታዊ ሁኔታ መረጃዎችን እንደማይለዋወጡ የገለፁ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

92. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ለተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Factsheet) እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በፅሁፍ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ሆስፒታሎች (ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆኑና ያልሆኑት) የሚገኙ የህክምና መሳሪያዎች ያሉበት ወቅታዊ ሁኔታ በMedical Equipment management information system (MEMIS) ሶፍትዌር በተዘረጋው ስርዓት መሰረት የሚከታተል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

93. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት በየሆስፒታሎች ያሉ መሳሪያዎች ወቅታዊ ሁኔታ በMedical Equipment management information system (MEMIS) ሶፍትዌር መሰረት ስለመከታተሉ የሚያሳይ ማስረጃ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃው ባለመቅረቡ እንዲሁም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር መረጃ አንቀያየርም ያሉ ሆስፒታሎች በመኖራቸው የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

94. በየሆስፒታሉ የሚገኙ የህክምና መሳሪያዎች ስለሚገኙበት ሁኔታ በየጊዜው የማስረጃ ልውውጥ አለመኖሩ የህክምና መሳሪያዎች ያሉበት ወቅታዊ ሁኔታ (የሚሰሩና የማይሰሩ፣ ጥገና የሚያስፈልጋቸው፣ በተጨማሪ የሚያስፈልጉ.......) እንዳይታወቁ እና በህክምና መሳሪያዎች አጠቃቀም ዙሪያ የሚከሰቱ ችግሮች በጊዜው እንዳይፈቱ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የህክምና መሳሪያዎችን በተመለከተ ከሆስፒታሎች እና ሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ማቀዱን በተመለከተ፤**

95. ሚ/ር መ/ቤቱ ከሆስፒታሎችና ሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የህክምና መሳሪያዎችን የሚመለከቱ ሥራዎችን በጋራ ሊያቅድና አፈጻጸሙን በጋራ ሊገመግምና ፣ በወቅቱ ግብረመልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡

96. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ስምንት የፌዴራል ሆስፒታሎች ውስጥ፡-

- ሁለቱ (የቅዱስ ጴጥሮስ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል እና የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ) የህክምና መሣሪያዎችን በተመለከተ ከጤና ሚኒስቴር ጋር በጋራ plan align እንደሚያደርጉ ነገር ግን አፈፃፀም በጋራ የማይገመግሙ መሆኑን የገለፁ ሲሆን እቅድ በጋራ ስለማቀዳቸው የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑ፣
- ቀሪዎቹ ስድስቱ (የጥቁር አንበሳ፣ የአለርት ስፔሻላይዝድ ኮምፕሬሲቭ ሆስፒታል፣ የጦር ሀይሎች ኮምፕርሂንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የፌዴራል ፖሊስ ጤና አገልግሎት ዋና መምሪያ፣ የጅማ ዩኒቨርስቲ ህክምና ማዕከል እና ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል) ዕቅድ በጋራ የማያቅዱ እና የማይገመግሙ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

97. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ለተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Factsheet) እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በፅሁፍ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ one plan one report በሚል ፕሮግራም ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ባካተተ መልኩ የህክምና መሳሪያዎችን የሚመለከቱ ሥራዎችን በጋራ የሚያቅድና አፈፃፀሙን የሚገመግም መሆኑን ገልፀዋል፡፡

98. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ እቅድና አፈፃፀምን በጋራ ስለማከናወናቸው በቃል ከመግለጽ ውጪ በጋራ ስለማቀዳቸው እና አፈጻጸሙን ስለመገምገማቸው እንዲሁም ስለተሰጠው ግብረ-መልስ የሚያሳዩ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

99. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሁሉንም ሆስፒታሎችንና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ባካተተ መልኩ እቅድና አፈፃፀሙን በየዓመቱ አለመገምገሙና በወቅቱ ግብረ-መልስ አለመስጠቱ በጤናው ዘርፍ ላይ የሚከሰቱ ችግሮች በወቅቱ እንዳይፈቱ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**ለባለሙያዎች የሚሰጥ የክህሎት ስልጠናን በተመለከተ፤**

100. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሕክምና መሳሪያዎች አጠቃቀም፣ አያያዝ፣ እና ጥገና በተመለከተ በእቅድ ላይ የተመሰረተ ለባለሙያዎች የክህሎት ስልጠና ሊሰጥ እና ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡

101. ይሁን እንጂ የህክምና መሳሪያዎች አጠቃቀም፣ አያያዝ እና ጥገናን በተመለከተ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጠና እንደሚሰጥ ነገር ግን ስልጠናው በቂ እና በሚፈለገው መጠን ስለመሆኑ እንዲሁም ያመጣውን ለውጥ በተመለከተ ክትትል እንደማይደረግ በኦዲት ወቅቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ ከሆኑ ሆስፒታሎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

102. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ለተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Factsheet) እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በፅሁፍ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጡ ስልጠናዎች ተግባራዊነት በሚያደርገው review meeting, mentorship እና ድጋፋዊ ጉብኝቶች የሚገመግም መሆኑን ገልፀዋል፡፡

103. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ የተሰጡ ስልጠናዎች ዝርዝርና የተደረጉ ግምገማዎችን የሚያሳዩ ማስረጃዎች እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

104. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በህክምና መሳሪያዎች ዙሪያ የሚሰጡ ስልጠናዎች በየጊዜው ተግባራዊ መደረጋቸውን እና ያመጡትን ለውጥ ክትትል አለማድረጉ ሰልጣኞች የመሳሪያዎችን መሰረታዊ ምንነት ተረድተው በስልጠናው መሰረት ለተጠቃሚዎች ትክክለኛውን አገልግሎት እየሰጡ ስለመሆናቸው በህክምና መሳሪያዎች ዙሪያ ያሉ ሌሎች ክፍተቶችን በመለየት ስልጠናዎችን ለማዘጋጀት እንዳይችሉ እንዲሁም ተጠቃሚዎች ከመሳሪያዎች ማግኘት ያለባቸውን ግልጋሎት በአግባቡ ማግኘት አለማግኘታቸውን ለማወቅ እንዳይቻል ሊያደርግ ይችላል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

105. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፌዴራል ሆስፒታሎች ህክምና መሳሪያዎች አገልገሎት አሰጣጥ በተመለከተ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚከናወንበት የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት የመደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡፡

- አገር አቀፍ የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ፖሊሲ፣ መመሪያ እና ስትራቴጂ አልተዘጋጀም፡፡
- ከአንድ የህክምና መሳሪያ ወደ ሌላ የህክምና መሳሪያ በመውሰድ እንደመለዋወጫ መጠቀም የሚያስችል መመሪያ በቅድሚያ ሳይዘጋጅ ሆስፒታሎች ከአንድ መሳሪያ እቃ ወስደው ወደ ሌላ መሳሪያ የሚገጥሙ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሆስፒታሎችን የህክምና መሳሪያ ፍላጎት በመጠየቅ እና በቅድሚያ በአመታዊ የግዥ እቅድ ውስጥ በማካተት ግዥ የማያከናውን መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመንግስት የጤና ተቋማት የህክምና መሳሪያዎች ግዥ ለመፈፀም የሚያስችል ስፔስፊኬሽን ያላዘጋጀ መሆኑ፣
- ከ2012-2014 ባሉት ዓመታት የስንት የሕክምና መሣሪያዎች ግዥ እና ለነማን ግዥው እንደተፈጸመ፣ የተገዙትም ለጤና ተቋማት (ሆስፒታሎች) የተላኩት የህክምና መሳሪያዎች ስለመድረሳቸው የሚያሳዩ ማስረጃዎች ያልቀረቡና በትክክል ስለመድረሳቸው ክትትል የሚያደርግበት ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል መንግስት ሥር ባሉ ሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን በቅንጅት አገልግሎት መስጠት የሚችሉበትን አሠራር ያልዘረጋ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ10 ዓመቱ የጤና ዘርፍ ዕቅድ መሠረት የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ለማድረግ የሚረዳ ዒላማና የድርጊት መርሃ ግብር ያላስቀመጠ መሆኑ፣
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ሁሉም ሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ (Medical Equipment Management Committee/MEMC) ያላቋቋሙና ሚኒስቴር መ/ቤቱ በለማቋቋም አለማቋቋማቸው ክትትል ያላደረገ መሆኑ፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ሆስፒታሎች በእርዳታ የሚገቡ የህክምና መሳሪያዎች ርክክብ ከመደረጉ በፊት በህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ ወይም በሆስፒታሎች ማኔጅመንት እየተረጋገጠ ርክክብ የሚደረግና የሚመዘገቡ መሆኑን የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች በስራ ላይ ያሉ ህክምና መሳሪያዎች መደበኛ የፍተሻ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ባለሙያ የደህንነት ፍተሻ (inspection and testing) እያስደረጉ ስለመሆኑ ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሳሪያዎች ለመሣሪያዎቹ በተቀመጠው የጊዜ መሰረት ትክክለኛነታቸውን በየጊዜው ለማረጋገጥ የመለካት (Calibration) ማከናወናቸው የማይረጋገጥ መሆኑ፣
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ሁሉም የመንግስት ሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሣሪያዎች ሲበላሹ የሚጠገኑበት የተደራጀ የህክምና መሣሪያዎች ማዕከል ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- ከአንድ የህክምና መሳሪያ አካል ወደ ሌላ የህክምና መሳሪያ በመውሰድ እንደመለዋወጫ መጠቀም የሚያስችል መመሪያ ሳይዘጋጅ የሚተገበር መሆኑ፣
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ሆስፒታሎች መወገድ ያለባቸው መሳሪያዎች አገልግሎት ከሚሰጡ እቃዎች ጋር በጋራ እና በየሆስፒታሎች ኮሪደርና ግቢ ውስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ሁሉም ሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎችን አስወግደው ስለማያውቁ የህክምና መሳሪያዎችን (ንብረቶችን) ከኢንቬንተሪ የማይሰረዙ መሆኑ፣
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ ሁሉም ሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎቻቸው ያሉበትን ወቅታዊ ሁኔታ (የሚሰራ፣ የማይሰራ፣ ጥገና የሚያስፈልግ ስለመሆኑ...) መረጃዎችን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር የማይለዋወጡ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህክምና መሣሪያዎችን በተመለከተ ከሆስፒታሎች ጋር እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በማቀድ አፈፃፀሙን የማይገመግም መሆኑ፣

➢ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሕክምና መሳሪያዎች አጠቃቀም፣ አያያዝ፣ እና ጥገና በተመለከተ የሚሰጣቸው የክህሎት ስልጠናዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን እና ያመጡት ለውጥ ስለመኖሩ ክትትል የማያደርግ መሆኑ፣

የሚሉ ናቸው፡፡

106. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

107. በኦዲቱ ወቅት የፌዴራል ሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገር አቀፍ የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ፖሊሲ፣ መመሪያ እና ስትራቴጂ አዘጋጅቶ በማጽደቅ፣ ለሚመለከታቸው አካላት በማሰራጨት ተግባራዊ ማድረጋቸውን በየጊዜው በእቅድ በመያዝ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሆስፒታሎችን የህክምና መሳሪያ ፍላጎት በመጠየቅ እና በመሰብሰብ በአመታዊ የግዥ እቅድ ውስጥ በቅድሚያ በማካተት ለመሣሪያዎቹ ተገቢውን ስፔሲፊኬሽን በማዘጋጀትና ግዥውን በተፈቀደው የግዥ ሥርዓትን በመጠቀም ግዥው መከናወኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ የተገዙትንም የህክምና መሣሪያዎች በተጠየቀው ስፔሲፊኬሽን መሠረት መሆኑን የሚረጋገጥበት ሥርዓት ሊዘረጋ፣ መሣሪያዎቹ ለጠየቁት አካል መድረሱን እና ርክክብ ተፈጽሞ በተቋማቱ ንብረትነት መመዝገቡን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል መንግስት ሥር ባሉ ሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን በቅንጅት አገልግሎት መስጠት የሚችሉበትን አሠራር በመዘርጋት ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ10 ዓመት የጤና ዘርፍ ዕቅድ መሠረት የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ለማድረግ የሚረዳ ግቦችና ኢላማዎችን በማስቀመጥና የድርጊት መርሃ ግብር የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍና በማዘጋጀት ወደ ትግበራ በመግባት በአገሪቱ ያለውን የህክምና መሣሪያዎች አቅርቦት ዕጥረት ሊቀርፍ እና አገሪቱ ለህክምና መሳሪያዎች ግዥ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ እንዲቀንስ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሁሉም የፌዴራል ሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ (Medical Equipment Management Committee/MEMC)


ስለማቋቋማቸው እና በመስራት ላይ ስለመሆናቸው በአመታዊ ዕቅድ ውስጥ አካቶ በመያዝ ክትትል እያደረገ ግብረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ሆስፒታሎች በእርዳታ የሚሰጡ የህክምና መሳሪያዎች ርክክብ ከመደረጉ በፊት በሆስፒታሎቹ የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ ወይም በሆስፒታሎች ማኔጅመንት እየተረጋገጠ ርክክብ የሚደረግ እና የሚመዘገብ መሆኑ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆስፒታሎች መሳሪያዎቻቸውን በዓመቱ በእቅድ በመያዝ የደህንነት ፍተሻ (inspection and testing) እያስደረጉ ስለመሆኑ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሳሪያዎች በትክክል እየሰሩ ስለመሆኑ በየጊዜው የማረጋገጥ የመለካት (Calibration) ሥራ እየተሰራ ስለመሆኑ በአመታዊ እቅድ እየያዘ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት ሆስፒታሎች የህክምና መሣሪያዎቻቸው ሲበላሹ የሚጠገኑበት የተደራጀ የህክምና መሣሪያዎች ማዕከል እንዲቋቋም ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየሆስፒታሉ መወገድ ያለባቸው የህክምና መሳሪያዎች አገልግሎት ከሚሰጡ እቃዎች ተለይተው እንዲቀመጡ እና የሚወገዱ የህክምና መሳሪዎችን በመመሪያው መሰረት በወቅቱ በማስወገድ ከኢንቨንተሪ የመሰረዝ ሥራ ስለመስራታቸው የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአንድ የህክምና መሳሪያ ወደ ሌላ የህክምና መሳሪያ እንደመለዋወጫ ለመጠቀም የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ያወጣቸውን የሕግ ማዕቀፎች መሰረት በማድረግ መመሪያ በቅድሚያ በማዘጋጀት ሆስፒታሎች እንዲጠቀሙበት በማሰራጨት ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየሆስፒታሉ ያሉ የህክምና መሳሪያዎች ወቅታዊ ሁኔታ (የሚሰሩ ወይም የማይሰሩ ስለመሆናቸው፣ ጥገና የሚያስፈልግ ስለመሆኑ ወዘተ) ማስረጃዎችን ከሆስፒታሎቹ ጋር ሊለዋወጥ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህክምና መሣሪያዎችን በተመለከተ ከሆስፒታሎች ጋር እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በማቀድና አፈፃፀሙን በመገምገም በህክምና መሳሪያዎች ዙሪያ የሚከሰቱ ችግሮች በወቅቱ እንዲፈቱ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሕክምና መሳሪያዎች አጠቃቀም፣ አያያዝ፣ እና ጥገና ዙሪያ የስልጠና ፍላጎት በመሰብሰብ በዓመታዊ እቅድ ይዞ ሊሰጥ እንዲሁም የሚሰጣቸው ስልጠናዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን እና ያመጡት ለውጥ ስለመኖሩ ክትትል በማድረግ በስልጠናዎች ላይ የሚከሰቱ ክፍተቶችን ሊፈታ ይገባል፡፡

በመጨረሻም ለጤና ሚኒስቴር መ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም በናሙና ተመርጠው ለታዩ ሆስፒታሎች ሃላፊዎች እና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1፡ የጤና ሚኒስቴር መዋቅር



# አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት:- የጤና ሚኒስቴር

የኦዲት አካባቢ ፡- የፌዴራል ሆስፒታሎች የሕክምና መሳሪያዎች አገልግሎት ለመስጠት የተዘረጋው የአሰራር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን፣

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| 1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽ፣ ጥራቱን የጠበቀና ቀልጣፋ እንዲሆን የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፣ | 1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገር አቀፍ የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ፖሊሲ አዘጋጅቶ በማፀደቅ ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሰራጭ እና ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- National medical device strategy report under situational anal |
| | 2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር መመሪያ እና ስትራቴጂ በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሰራጭ እና ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የ2014 የህክምና መሳሪያዎች ዳይሬክቶሬት አፈፃፀም ሪፖርት HSTG) August, 2017 Ethiopian Hospital Management Initiative Version 1.0- Page-27-28 |
| | 3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎችን ለማስወገድ የሚረዳ ማንዋል ወይም መመሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በማዘጋጀትና ለሚመለከታቸው ፈጻሚ አካላት በማሰራጨት ተግባራዊ መደረጉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- (HSTG) August, 2017 1.0- Page-12፣ 17 C፣ 21 እና 47፣ National medical device strategy report under Decommissioning and Disposal |
| | 4. የህክምና መሳሪያዎች ግዥ በዕቅድ መሰረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡<br>ምንጭ- የጤናው ዘርፍ የአስር አመት የልማት እቅድ ከ2013-2022 ዓ.ም መስከረም 2014 ዓ.ም ገፅ 22) |
| | 5. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመንግስት የጤና ተቋማት የህክምና መሳሪያዎች ግዥ ለመፈፀም የሚያስችል ስፔስፊኬሽን ሊዘጋጅ እና አስፈላጊው የጨረታ ዘዴ ተመርጦ ግዥ ሊከናወን ይገባል፡፡<br>ምንጭ- የጤናው ዘርፍ የአስር አመት የልማት እቅድ ከ2013-2022 ዓ.ም መስከረም 2014 ዓ.ም ገፅ 22) እና የ2011 የህክምና መሳሪያዎች ዳይሬክቶሬት አፈፃፀም ሪፖርት |
| | 6. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህክምና መሰሪያዎች ግዥ ለጠየቁት አካላት መድረሱን የሚረጋገጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ- የጤናው ዘርፍ የአስር አመት የልማት እቅድ ከ2013-2022 ዓ.ም መስከረም 2014 ዓ.ም ገፅ 22) እና የ2011 የህክምና መሳሪያዎች ዳይሬክቶሬት አፈፃፀም ሪፖርት |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | 7. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመንግስት ሥር ባሉ ሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን በቅንጅት አገልግሎት መስጠት የሚችሉበትን አሠራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡ የአገሪቱ የ10 አመት የልማት ዕቅድ ፍኖተ ብልጽግና 2013-2022፣ ገጽ 146 |
| | 8. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- ከ2013 ዓ.ም እስከ 2022 ዓ.ም የጤናው ዘርፍ የአስር አመት ልማት እቅድ ገፅ-22፣ |
| | 9. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህክምና መሳሪያዎች ተከላና ኮሚሽኒንግ (installation and commissioning) ስታንዳርድ በማዘጋጀት ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተል እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- National medical device strategy report under Installation, Commissioning, Maintenance and Utilization |
| 2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሣሪያዎች በአግባቡ እየሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣ | 10. የህክምና መሳሪያዎች ተከላ ከመከናወኑ በፊት የቅድመ ተከላ ስራ (Pre-installation work) መሰራቱን የሚረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- Medical Device Distribution Protocol Ministry of Health March, 2021 Version I Page-3 |
| | 11. በሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎችን ሁኔታ የሚከታተል የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ (Medical Equipment Management Committee/MEMC) ሊቋቋም እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም መቋቋማቸውን የሚከታተልበት ስርዓት ዘርግቶ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- (HSTG) August, 2017 Ethiopian Hospital Management Initiative Version 1.0- Page-16 እና 17 |
| | 12. ለፌዴራል ሆስፒታሎች በእርዳታ የሚገቡ የህክምና መሳሪያዎች ርክክብ ከመደረጉ በፊት በህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ ወይም በሆስፒታሎች ማኔጅመንት ሊረጋገጡና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህን የሚከታተልበት ስርዓት ዘርግቶ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- (HSTG) August, 2017 Ethiopian Hospital Management Initiative Version 1.0- Page-31 እና 32 |
| | 13. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች በስራ ላይ ያሉ ህክምና መሳሪያዎች መደበኛ የፍተሻ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ባለሙያ የደህንነት ፍተሻ (inspection and testing) ሊደረግላቸው ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- (HSTG) August, 2017 Ethiopian Hospital Management Initiative Version 1.0- Page-12 እና 40-48 |
| | 14. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመንግስት ሆስፒታሎች ያሉ የህክምና መሳሪያዎች በስታንደርዱ መሰረት ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የመለካት (Calibration) ሊደረጉ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- (HSTG) August, 2017 Ethiopian Hospital Management Initiative Version 1.0- Page-1 እና 40-48 |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | 15. በመንግስት ሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሣሪያዎች ሲበላሹ የሚጠገኑበት የተደራጀ የህክምና መሣሪያዎች ማዕከል ሊቋቋም ይገባል፡፡ <br> **ምንጭ፡-** ሁለተኛው የጤናው ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ 2013 ዓ.ም - 2017ዓ.ም ገፅ-59፣ (HSTG) August, 2017 Page-12፣13 እና 17 |
| | 16. ሆስፒታሎች የተበላሹ እና ጥገና የሚያስፈልጋቸውን የህክምና መሳሪዎች በአፋጣኝ ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል፡፡ <br> **ምንጭ፡-** (HSTG) August, 2017 Ethiopian Hospital Management Initiative Version 1.0- Page- 18 እና 23 |
| | 17. ከየሆስፒታሎች የሚወገዱ የህክምና መሳሪያዎች ተለይተው ሊቀመጡ ይገባል፡፡ <br> **ምንጭ፡-** National medical device strategy report under Weaknesses |
| | 18. የተወገዱ የህክምና መሳሪያዎች ከኢንቨንተሪ ዝርዝር ላይ የተሰረዙ መሆናቸውን የሚረጋግጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ <br> **ምንጭ፡-** (HSTG) August, 2017 Ethiopian Hospital Management Initiative Version 1.0- Page-47 እና 48 |
| | 19. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሳሪያዎች ያሉበት ወቅታዊ ሁኔታ (በስራ ላይ ስለመሆን አለመሆናቸው፣ ጥገና የሚያስፈልግ ስለመሆኑ ወዘተ) የሚከታተልበት ሥርዓት ሊዘረጋ እና መረጃ ሊይዝ ይገባል፡፡ <br> **ምንጭ፡-**Medical Device Distribution Protocol Ministry of Health March, 2021 Version I Page- 5-6 and (HSTG) August, 2017 Page-13 እና 18 |
| 3. **ሚኒስቴር መ/ቤቱ በህክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ከሆስፒታሎች እና ሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ያለው የመረጃ ልውውጥ እና ቅንጅታዊ አሰራር ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣** | 20. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሳሪያዎችን መረጃዎች በመያዝ መረጃ የሚያዝበትና ልውውጥ የሚደረግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ <br> **ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ** |
| | 21. ሚ/ር መ/ቤቱ ከሆስፒታሎችና ሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የህክምና መሳሪያዎችን የሚመለከቱ ሥራዎችን በጋራ ሊያቅድና አፈጻጸሙን በጋራ ሊገመግም ፣ ግብረመልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ <br> **ምንጭ፡ መልካም ተሞክሮ** |
| | 22. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሕክምና መሳሪያዎች አጠቃቀም፣ አያያዝ፣ እና ጥገና በተመለከተ በእቅድ ላይ የተመሰረተ ለባለሙያዎች የክህሎት ስልጠና ሊሰጥ እና ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡ <br> **ምንጭ፡- የጤና ሚኒስቴር መዋቅራዊ ማሻሻያ ሰነድ የመድሀኒት፣ ሕክምና መሳሪያዎች እና መገልገያዎች ዋና ስራ አስፈጻሚ ዋና ዋና ተግባራት** |
| | 23. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት ሆስፒታሎች የሌሎች በተለይ የግል ተቋማትን የህክምና መሳሪያዎች ለመጠቀም/ አገልግሎት ለማግኘት የሚችልበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ <br> **ምንጭ፡ መልካም ተሞክሮ** |

## አባሪ 3፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ ሆስፒታሎች ዝርዝር

1. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል
2. አለርት አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል
3. በመከላከያ ሚኒስቴር የጦር ሃይሎች ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝ ሆሰፒታል
4. ቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል፣
5. ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል፣
6. ፌዴራል ፖሊስ ጤና አገልግሎት፣
7. የወልቂጤ ዩኒቨርሲቱ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና
8. የጅማ ዩኒቨርሲቱ ህክምና ማዕከል